# ወ/ት ብርቱካን «ጀግና አይወለድብሽ» ብላ ኢትዮጵያን ትረግም ይሆን?

ግርማ ካሳ
(muziky68@yahoo.com)

ሐምሌ 20 ቀን 2002

ያኔ በዘጠና ሰባት በኢትዮጵያ የተፈጠረዉን መልካም የፖለቲካ ማእበል ወቅት ተመልክቼ በጣም ተደስቼ ነበር። ኤርትራን በማስገንጠላቸዉና የዘር ፖለቲካን በማስፋፋታቸዉ በኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ላይ ትልቅ ችግር ቢኖረኝም፣ ያን አይነቱ የዴሞክራሲ እንቅስቃሴ በአገራችን እንዲመጣ በማድረጋቸዉ ግን፣ ትልቅ ከበሬታ ሰጥቻቸዉ ነበር። (በነሸብሬ ደሳለኝ ላይ የደረሰዉን አሳዛኙን ግፍ በአይኔ እስካየሁበት ጊዜ ድረስ)

አምስት አመታት አለፉ። ከዘጠና ሰባት ምርጫ እስከ ሁለ ሺህ ሁለት ምርጫ የነበሩትን አመታት ወደ ኋላ ተመልሼ ማሰብ ጀመርኩ። ፈገግታ ከፊቴ ጠፋ። ዉስጤ ሃዘን ሞላዉ። ለስድስት ወራት በጨለማ እንድትቀመጥ የተደረገች፣ ለሕዝብ ነጻነት ስትል እስከ አሁን ድረስ በቃሊቲ የምትሰቃየዉ እህቴ ብርቱካን ሚደቅሳ በፊቴ ድቅን አለች። ለፍትህ ለእዉነት ነዉ የቆመችዉ። ለአገር ሰላምና እርቅ ስትል በአገር ሽምግልና ወግ መሰረት ይቅርታ መጠየቋን አልካደችም። ነገር ግን የዘመኑ ሰዎች የግፍ በተር አሳረፉባት። አሁንም ብርቱካን ሚደቅሳ በቃሊቲ ናት። አሁንም የግፈኞችን ዱላ እየቀመሰች ነዉ። አሁንም ሕክምና ተነፍጋ ትሰቃያለች።

«ለዴሞክራሲ ቆሚያለሁ፣ የሰብአዊ መብት መከበርን በተመለከተ ከቡሽ የተሻልኩ ነኝ» ያለዉ፣ እንዲመረጥ በብዙዎቻችን ትልቅ ድጋፍ የተደረገለት ባራክ ኦባማ፣ እንኳን ብርቱካን ሚደቅሳ እንድትፈታ ግፊት ሊያደርግ ቀርቶ፣ ከአሳሪዎቿ ጋር ሲሳሳቅና ሲተቃቀፍ እያየነው ነዉ። በአክራ በካይሮ በዋሺንገት ሲነገረን የነበረዉ ነገር ሁሉ ወሬና ቃላት ብቻ መሆኑ ተመሰከረ።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ መሪ ነበረች። አሁንም ናት። እርሷ ስትታሰር የሥራ ባልደረቦቿ ፈለጓን ይከተላሉ ተብሎ ሲጠበቅ፣ በፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም የሚመራዉ የዝም አንልሞች ቡድን በፈጠረዉ ቀዉስ፣ የብርቱካን ፓርቲ ክፉኛ ተጎዳ። ይህ ቡድን ያለዉን ችግር በፓርቲዉ ዉስጥ ባሉ መድረኮች ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መፍታት ሲገባዉ፣ ከሌሎች አመራር አባላት ጋር ያለዉን ውዝግብ ይፋ አወጣዉ። የብዙዎቻችንን አንገት አስደፋ። ከእሥር ቤት የምትማቅቀዋን ብርቱካን ሚደቅሳን ልብ ወጋ። በቃሊቲ ከደረሰባት የአካል ጉዳት የበለጠ በአንድነት ፓርቲ ዉስጥ የተፈጠረዉ ችግር ዉስጧን እንደሚሰብር መገመቱ አይከብድም።

ጋንዲ ሲታሰር፣ ኔልሰን ማንዴላ ሲታሰር፣ ህዝብ ተንቀሳቅሷል። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ስትታሰር ግን እንደሚጠበቀዉ ህዝብ ሊነሳ አልቻለም። ሁሉም በዉስጡ ይናደዳል። ሁሉም በቤቱ ያለቅሳል። ሁሉም ከንፈር ይመጣል። ነገር ግን ከዚያ ያለፈ ነገር አልታየም።

ከሌሎች የቅንጅት መሪዎች ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ታስራ የተፈታቸዉ ለአሥራ ስምንት ወራት በተደረገ የ«ሽምግልና» ጥረት ነበር። ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይሳእቅ እንዲሁም በርካታ «የአገር ሽማግሌዎች ነን» የሚሉ፣ እሥረኞች የተፈቱበትን ሁኔታ ጠንቅቀዉ ያውቃሉ። ነገር ግን የዘመኑ ሰዎች «ይቅርታ አልጠየቹም» ብላለች ብለዉ ርካሽ በሆነ ምክንያት ሲያስሯት፣ እነዚህ ሽማግሌዎች እዉነትን ከመናገር ተቆጠቡ። እነርሱ ዝም በማለታቸዉ፣ እዉነትን ለመናገር ባለመፈለጋቸዉ፣ እዉነተኛ ሽማግሌዎች ሳይሆኑ የዘመኑ ሰዎች ተላላኪ መሆንን በመምረጣቸዉ፣ ብርቱካን ሚደቅሳ ይኸዉ እየማቀቀች ነዉ። ሊመሰክሩ የሚችሉት እነርሱ ነበሩ። «አይደለም። ብርቱካንና የተናገረችዉ ትክክል ነዉ» ቢሉና እዉነትን ቢናገሩ ምናልባትም ኢሕአዴጎች ብርቱካንን ላያስሯት ይችሉ ነበር።

በውጭ አገር ያለን ኢትዮጵያውያንም የተከፋፈልን ነን። ኢሕአፓ፣ ኢሕአፓ - ዴሞክራሲያዊ፣ ግንቦት ሰባት፣ ሕብረት፣ ኦነግ፣ ኢሕአዴግ እንዲሁም ቆጥሬ የማልጨርሳቸው የሲቪክ ማህበራት አሉ። ሁሉም መተባበር አለብን ይላሉ። ግን የሚተባበር የለም። ከተሳሳትኩ ለመታረም ዝግጁ ነኝ።

ኢትዮጵያውያን ነን። ሁላችንም በአገራችን ሰላም እንዲሰፍን፣ ሕግ የበላይ እንዲሆን እንፈልጋለን። ብርቱካን ሚደቅሳ እንድትፈታ ጉጉታችን ነው። ነገር ግን በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ተሰባስበን፣ በተወሰኑ፣ መስማማት በምንችልባቸው ቁም ነገሮች ዙሪያ እንኳን አብረን መሥራት አልቻልንም።

እንግዲህ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ በአሜሪካ ባለስልጣናት፣ በአንዳንድ የሥራ ጓዶቿዋ ክህደት እንደደረሰባት አይተናል። ብርቱካን ሚደቅሳ ቆሜለታለሁ ያለችው ህዝብ፣ የተወሰነው በገንዘብ ተገዝቶ፣ የተወሰነው ፈርቶ ሊነሳላት አልቻለም። «ብርቱካን ብርቱካን» የምንለው በውጭ አገር ያለነውም ኢትዮጵያዊንም፣ እንደሚጠበቅብን ተባብረን ተንቀሳቅሰናል ለማለት ይከብዳል። ብርቱካንን ለማስፈታት፣ በአገራችን ለሚደረገው ትግል ትልቅ አስተዋጽኦ ለማድረግ የግድ መተባበር ያስፈልጋል። ኢትዮጵያዊው ሊተባበር አልቻለም። መጠላለፍ፣ አንዱ ሌላውን ማጥቃት ሆኗል ተግባሩ።

ደጃች በላይ ዘለቀ ይሁኑ ጄነራል መንግስቱ ንዋይ፣ በአጼ ኃይለስላሴ ስቅላት ሲደርስባቸው ኢትዮጵያን በማሰብ «ጀግና አይወለድብሽ» ብለው እንደነበረ ሰምቻለሁ። ለአገር እድገትና ነጻነት ሲሉ ለሞት መዳረጋቸውና ሕዝቡም ዝም ማለቱ አሳዝኗቸው ሳይሆን አይቀረም ኢትዮጵያን ረግመዋት የሞቱት።

በርግጥ የነዚህ ጀግኖች እርግማን አልደረሰብንም። ኢትዮጵያ እንደ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ያሉ ጀግኖችን ወልዳለች። ነገር ግን ብርቱካን ሚደቅሳ ለሕዝብ እድገትና ነጻነት ስትል ስቃይ ሲደርስባት፣ ሳትታሰር በፊት ሆ ሲልላት የነበረው ህዝብ ዝም ማለቱ አሳዝኗት፣ እርሷም እንደነ በላይ ዘለቀና እንደ ጄነራል መንግስቱ ንዋይ «ጀግና አይወለድብሽ!» ብላ ኢትዮጵያን ትረግም ይሆን ?

ይህስ አይሁን ! ጀግኖቻችንን አስበልተን፣ ምንም እንዳልሆነ ቆጥረን፣ የምንኖር ሰዎች አያድርገን። ተባብረን፣ የአስተሳሰብና የአመለካከተ ተሃድሶ አድርገን፣ ያሉንን ልዩነቶች ወደ ጎን በማድረግ፣ በምንችለው አቅም ሁሉ ለዚች ክቡር ሴት መፈታት ያለንን ድርሻ እንወጣ። «በትንሹ ያልታመነ በብዙ አይሾምም» እንዳለው ታላቁ መጽሃፍ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለሕዝቧ ነጻነት ቆመናል እያልን ለነብርቱካን ሚደቅሳ ካልቆምን እንዴት ኢትዮጵያን ለማዳን የተነሳን ነን ማለት እንችላለን ? ኢትዮጵያን ማዳን የሚጀመረው ለኢትዮጵያ ሲሉ የታሰሩትን በማስፈታት ነው !

«እሺ ምንድን ነው ማድረግ ያለብን?» የሚል ጥያቄ አንዳንዶቻችን ልናነሳ እንችላለን። «ከልብ ካለቀሱ እንባ አይገድም» ይላሉ አባቶቻችን። ቁጭ ብለን «እኔ ምን ማድረግ እችላለሁ? » ብለን በቁም ነገር እራሳችንን ብንጠይቅ ብዙ ማድረግ የምንችላቸው ነገሮች እንዳሉ እንገነዘብ ነበር። ቢያንስ ቢያንስ በእግዚብሄር ፊት በጸሎት ተደፍተን «አቤቱ ጌታ ሆይ፣ ግፍ እየደረሰባት ያላችውን እህታችንን አስባት » ብለን መትጋት እንችላለን። ጥያቄው «የሚሰራው ምንድን ነው ?» የሚለው ሳይሆን «የመስራት ፍላጎቱና ቁርጠኝነቱ አለ ወይ?» የሚለው ነው።

እንደ ሰው የሚረሳና የሚተው ያልሆነ እግዚአብሄር ባለችበት ቦታ በመንፈስም በስጋም ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ይጎብኛት። ብርታቱን፣ መጽናናቱንና ጥንካሬውንም ይስጣት። ቤተሰቧንም ይባርክ።ለተጠቃው ለተጎዳው የማያስብባ፣ የማይቆረቆር ሰውና ሌላው ሲጠቃ ዝም የሚል ሰው፣ እርሱ ሰው አይደለም። እግዚአብሄር ሰዎች ያድርገን !